**ቁጥር ሲሰኮ30/ጠ10/92/180**

**ቀን ማስከረም 8/2012**

**ዓ.ም**

# የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

**የነጥብ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት የደመወዝ**

**ስኬል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 36/2013**

ማስከረም 8/2012ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ"**የነጥብ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት የደመወዝ ስኬል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 36/2013**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1) «**የደመወዝ/ስኬል ማሸጋገሪያ**» ማለት የአንድን ሠራተኛ ደመወዝ ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል ለማሸጋገር ሲባል ቅርበቱ እየታየ የነበረውን ደመወዝ እንደሁኔታው ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል የማሻ፣የእርከን ወይም የጣሪያ ደመወዝ ላይ ለማሳረፍ የሚፈቅድ የደመወዝ ስኬል ማሸጋገሪያ ነው፡፡

2) «**ኮሚሽን**»ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡

3) «**የማሸጋገሪያ ደመወዝ**»ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ማስረት አንድ ሰራተኛ በደመወዝ ስኬል ሽግግሩ የሚያገኘውን የደመወዝ ስኬል ማሸጋገሪያ ማጠን ለሶስት በማካፈል መደበኛ ደመወዙ ላይ ጨምሮ እስከ ሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ድረስ የሚከፈል ደመወዝ ነው፡፡

### 3. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተግባራዊ የሚደረገው የሥራ መደቦቻቸው በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ በወጣላቸው የሥራ መደቦች ላይ ለተደለደሉ ሠራተኞች ብቻነው፡፡

### 4. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ወስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

### 5. ልዩ ልዩ ወሳኔዎች

**1) በስራ ላይ የሚቆየው የደመወዝ ስኬል**

የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት እና የመንግስት የመክፈል አቅም ግምት ወስጥ ገብቶ የተቀረጸወና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተወሰነው የደመወዝ ስኬል በሁሉም የመንግስት ማስሪያ ቤቶች ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የዚህ መመሪያ አባሪ ሆኖ ተያይዟል፡፡

2) **ወደፊት ልዩ የደመወዝ ስኬል የማይፈቀድ ስለመሆኑ**

የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት በሀገር አቀፍ ደረጃ መተግበሩን ተከትሎ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ያሉ የደመወዝ ስኬሎችን ወደ አንድ የሚሰባሰብ ተግባር ስርአቱ ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ጸንቶ ማጠበቅ ስላለበት መንግስት አገር አቀፍ የደመወዝ ስኬል ማዘርጋት ስርአትን የልዩ የደመወዝ ስኬል ይፈቀድልኝ የሚሸረሽር ጥያቄን የማያስተናግድ ስለመሆኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተላለፈው ወሳኔ የጸና ሆኖ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**3) ተጨማሪ ወጪን በሶስት የበጀት ዓመታት ስለማሸፈን**

ከነባሩ የሥራዎች ምዝና ስርዓት ወደ ነጥብ የሥራዎች ምዝና ዘዴ የሚደረገው ሽግግር ዓላማ ለሠራተኞች የደመወዝ ማስተካከያ ወይም ጭማሪ ማድረግ አይደለም፡፡ ሆኖም ሽግግሩ በአንዳንድ የሥራ መደቦች ላይ የደመወዝ ለወጥ ስለሚያስከትል በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ የሚፈረወን የወጪ ጫና ከመንግስት የመክፈል አቅም ጋር ተገናዝቦ በመቋቋም የደመወዝ ስኬል ሽግግሩን ቀለል ባለ መንገድ ለሚፈጸም ዝርዝር የአከፋፈል ሁኔታው፦ –

ሀ) በተደለደሉበት የሥራ መደብ ብር 1,000 እና ከዚህ በታች የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ የሚያገኙ ሠራተኞች ሙሉ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያወን በአንድ ጊዜ እንዲያገኙ፣

ለ) ከብር 1,000 በላይ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ የሚያገኙ ሠራተኞችልዩነቱንበሶስት እኩልክፍያዎች እንዲጠናቀቅላቸው፣

ይደረጋል፡፡

**4) በዚህ ጥናት ያልተካተቱ ተቋማት**

የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣የጉምሩክ ኮሚሽን እና የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ከደመወዝ ስኬል ሽግግር ወሳኔ በፊት ተፈቅዶላቸው በነበረው የደመወዝ ስኬል እየተጠቀሙ ይቆያሉ፡፡ ሆኖም ይህ የሽግግር ጊዜ የደመወዝ ስኬል በመንግስት ወሳኔ ማስረት ወደፊት ሲሻሻል የተቋማቱ የደመወዝ ስኬል የሚከተት ሆኖ ሲገኝ የየተቋማቱ የደመወዝ ስኬል እንደሌሎቹ የፌዴራል ተቋማት በሀገር አቀፉ የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል ወስጥ የሚከተት ይሆናል፡፡

**5) ሁሉም የመንግስት ባለበጀት ተቋማት በደመወዝ ስኬል ሽግግሩ ስለመካተታቸው**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዐስ አንቀጽ 4ከተመለከቱ ተቋማት በስተቀር ሁሉም የመንግስት ባለበጀት ማስሪያቤቶች በደመወዝ ስኬል ሽግግሩ የሚከተቱ ይሆናል፡፡ ይህ የደመወዝ ስኬል

ሽግግር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ እያለ የምዝና ማጥራት ስራ እተካሄደባቸው የነበሩ በመምህራን፣ በርእሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች የስራ መደቦች ላይ ያሉ ሰራተኞች እንደማንኛውም የማግሥት የደመወዝ ስኬል ሽግግሩ ወጤቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

**6) ክፍያው ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜ**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዐስ አንቀጽ 3 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ በነጥብ የስራ ምዝና ዘዴ ደረጃ ለወጣላቸው የስራ መደቦች ክፍያው ከሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

# የደመወዝ ስኬል ሽግግር ዝርዝር አፈጻጸም

6. ከነባሩ የሥራዎች ምዘና ሥርዓት ወደ ነጥብ የሥራዎች ምዘና ዘዴ የሚደረገዉን የደመወዝ ስኬል ሽግግር አፈጻጸም ከዚህ በታች በተመለከተው መስረት ይሆናል፡፡

1) የነባር የሥራ መደብ ማጠሪያና ደረጃ በአዲስ ማጠሪያና ደረጃ መቀየሩን የሚያረጋገጥ የማሻጋገሪያ ሠንጠረዥ ከኮሚሽኑያልደረሰው ተቋም የሠራተኛ ድልድል ሚፈጸምም ሆነ የደመወዝ ማስተካከያ ሚድረግ አይቻልም፡

2) በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ በተመዘኑ የሥራ  መደቦች ላይ የሚፈጸም ድልድል ከተፈጸመ በኋላ በተካሄደ የአደረጃጀት ለውጥ ወይም ሌላ ምክንያት ዳግም መመዘን ባለበት የሥራ መደቦች ላይ የተደለደለ ሠራተኛ ክፍያዉን እንዲያገኙ የሚደረገው በቅድሚያ ሥራ መደቡ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከጸደቀ በኋላ ነው፡፡

3) በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝነው ደረጃ በወጣላቸው የሥራ መደቦች ላይ የተደለደሉ ሠራተኞች ለተመደበብት ደረጃ የተወሰነዉን ደመወዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3በተመለከተው መሠረት ከአዲሱ የደመወዝ ስኬል ጣሪያ ሳያልፍ ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም ጀምሮ ይከፈላቸዋል፡፡

4) የነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ የማንግስት ሠራተኞች ድልድል አፈጻጸም መመሪያ የሚጠይቀዉንማስፈርትማሟላታቸው ተረጋግጦ ድልድል የጸደቀላቸው ሠራተኞች፡-

   ሀ) የመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ኡደት አይለወጥም፣

   ለ) ለደረጃ እደገት የአንድ ዓመት መቆያ ጊዜአይጠበቅበትም፣

5) ከነባሩ የሥራዎች ምዘና ዘዴ ወደ ነጥብ የሥራዎች ምዘና የሚደረገዉን ሽግግር ተግባራዊ ለማድረግ በተደረገ የሠራተኞች ድልድል ሠራተኛዉየያዘው የሥራ መደብ በእንደገና ምደባ ከፍ ብሎ ከተመደበ የሥራ መደቡን የያዘው ሠራተኛ ማስፈርቱን እስካሟላ ድረስ የሥራ መደቡ የሚያስገኘዉን ደረጃና ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

6) ከፍ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ በተጠባባቂነት የተመደበ ሠራተኛ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ ልዩነትየሚታሰብለት በድልድሉ በተመደበበት ደረጃ ላይ ነው፡፡

7) በጥር ወር 2009 ዓ.ም ተሻሽሎ በሥራ ላይ በዋለው የደመወዝ ስኬል ጣሪያ ላይ የደረሰና በአዲሱ የደመወዝ ስኬል ጣሪያው የሚሳለት ሠራተኛ በተመደበበት የሥራ ደረጃ የአዲሱን የደመወዝ ስኬል ጣሪያ ሳያልፍ ማስተካከያዉን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

8) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) አንድ ሠራተኛ የሚከፈለው ደመወዝ በደመወዝ ስኬሉ ለተደለደለበት የሥራ መደብ ከተወሰነው የመነሻ ደመወዝ በታች ከሆነ፤ የሠራተኛው ደመወዝ ወደ መነሻ ደመወዝ ከፍ እንዲል ይደረጋል።

ለ) የሠራተኛው ደመወዝ ከመነሻ በላይ ሆኖ፤ በመነሻና በአንደኛው የእርከን ደመወዝ መካከል ወይም በሁለት የእርከን ደመወዞች መካከል ከሆነ በአቅራቢያው ወደ አለው ከፍ ያለ የእርከን ደመወዝ ይስተካከላል።

ሐ) የሠራተኛው ደመወዝ ከደመወዝ ስኬሉ የመነሻ፣ የእርከን ወይም የጣሪያ ደመወዝ ጋር ከገጠመ ወይም ከጣሪያ በላይ ከሆነ የያዘውን ደመወዝ እንደያዘ ይቀጥላል ።

9) ኮሚሽኑበአንድ ተቋም ከተፈጸሙ የሠራተኞች ድልድል መካከል በተለያዩ ሕግን ባልተከተሉ አሠራሮች ምክንያት ያልተቀበለው ካለ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ጭማሪው የሚሰጠው በድልድል አፈጻጸም መመሪያው መሠረት ሠራተኛው በሚመደብበት ደረጃ ከተደለደለ በኋላ ነው፡፡

10) ከፍ ከላ የሥራ ደረጃ ላይ በሚያስብ ደመወዝ ተቀጥሮ እየተቀነሰ የሚከፈለው ሠራተኛ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ተጠቃሚ የሚሆነው በሚመደብበት ደረጃ ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡፡

11) በመካራ ቅጥር ላይ የሚገኝ ሠራተኛ የዚህ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

12) በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያት ከደረጃው ዝቅ ያለና ደመወዙ የተቀነሰበት ሠራተኛ ማስተካከያው የሚሰጠው በተቀነሰው ደረጃና ደመወዝ ላይ ታስቦ ነው፡፡ ሆኖም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ የተደረገ ሠራተኛ የጊዜ ገደቡ ደርሶ ወደ ቀድሞ ደረጃው ሲመለስ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ በአዲሱ የደመወዝ ስኬል ተገቢው ደመወዝ ይሰጠዋል፡፡

13) ተቋሙ ፈቅዶለት አንድ ዓመትና በላይ በሚፈጅ ትምህርት ወይም ሥልጠና ላይ ያለ ሠራተኛ በድልድል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 7.7 መሠረት ለተመደበበት የሥራ ደረጃ የተወሰነው አዲሱ ደመወዝ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3መሠረት ይከፈለዋል።

14) ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶት በፕሮጀክት የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት ወደ ፕሮጀክት የተዛወረሠራተኛ፡ –

ሀ) መደበኛ ደመወዙ በነበረበት መሥሪያቤት የሚከፈለው ከሆነ ወደ ፕሮጀክት ከመዛወሩ በፊት የነበረ መደበኛደመወዙን መሠረት በማድረግ ለተደለደለበት የሥራ ደረጃ የተወሰነው አዲሱ ደመወዝ ተጠቃሚ ይሆናል።

ለ) ደመወዙ ከፕሮጀክቱ እየተከፈለው የሚሠራ ከሆነ ወደ መደበኛ ሥራው ሲመለስ ለሚደለደልበት የሥራደረጃ የተወሰነው አዲሱ ደመወዝ ተጠቃሚ ይሆናል።

15) ይህ የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሠራተኛን አይመለከትም፡፡ ሆኖም በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝኖ ደረጃ በወጣለት ቋሚ የሥራ መደብ ላይ መመሪያውን ተከትሎ የተቀጠረ ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሠራተኛ የደመወዝ ማስተካከያው ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

16) በተለያዩ ምክንያቶች ከመደበኛ ሥራው ተለይቶ የቆየ ሠራተኛ ወደ ሥራው እንዲመለስ ሲደረግ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝኖ ደረጃ በወጣለት የሥራ መደብ ላይ እንዲመደብ ከተደረገ በኋላ ደመወዙ ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡

17) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3ወሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ይህ መመሪያ እስከወጣበት ቀን ድረስ ከሥራ የለቀቀ ሠራተኛ ከሥራ እስከተለየበትቀንድረስ ያለው ደመወዙ በአዲሱ የደመወዝ ስኬል መሠረት ተሰልቶይከፈለዋል፡፡

ለ) ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም አስከ ማከረም ወር 2012 ዓ.ም በሞት የተለየ ሠራተኛ በሞተበት ወር ደመወዙ በአዲሱ የደመወዝ ስኬል መሠረት ተሰልቶ ለወራሾቹ ይከፈላል፡፡

ሐ) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) ቢኖርም ከሐምሌ ወር 2011 ዓ.ም ጀምሮይህ መመሪያ አስከወጣበት ቀን ድረስ በሞትየተለየ ሠራተኛ ከብር 1000 በላይ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ ልዩነት የሚገኝ ከሆነ በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተመደበበት የስራ ደረጃ የአዲሱ የደመወዝ ስኬል ማነሻ ጣሪያ ደመወዝ የሶስት ወር ደመወዝ በአንድ ጊዜ ለወራሾቹ ይከፈላል፡

18) መሥሪያ ቤቱ ባወቀው በማኝቸውም ምክንያት በድልድል ወቅት ሥራ ላይ ባለመኖሩ ያልተደለደለ ሠራተኛ ቅድሚያ በሥራ ላይ ባሉ መመሪያዎች መሠረት ወደ ምድብ ሥራው እንዲመለስ ሲደረግ በነጥብ የሥራ ምዘና ዘዴ ተመዝኖ ደረጃ በወጣለት ሥራ መደብ ላይ እንዲመደብ በማድረግ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያው ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

19) በድልድል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 7.12 "አንድ ሠራተኛ ለአንድ የሥራ መደብ የተቀመጠውን የሥራ ልምድ ለማሟላት እስከ አንድ ዓመት ከጐደለው እና ለሥራ መደቡ የተቀመጠውን የተፈላጊ ችሎታ የሚያሟላ ሌላ ሠራተኛ ከሌለ ሠራተኛውን ደልድሎ ማሠራት ይቻላል፡፡" በሚለው መሠረት ለተደለደለበት ደረጃ እስከ አንድ ዓመት የሚጎድለው ሠራተኛ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ ጭማሪ ተጠቃሚ የሚሆነው የተደለደለበት የሥራ መደብ የሚጠይቀውን ቀሪ የሥራ ልምድ ሲያሟላ ነው፡፡

20) በሥራው ልዩ ባህርይ ምክንያት እያስተማሩ የህክምና አገልግሎት የሚያበረክት የጤና ባለሙያ የሚያስተምር ሥራው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደሁኔታው በአካዳሚክ ወይም በጤና ሙያ /ከፍ ባለው/ ደረጃ ላይ ተደልድሎ ሊሠራ ይችላል፡፡

21) በዚህ መመሪያው አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በነባሩ የጤና ባለሙያዎች የእድገት መሰላል በሙያው የሚጨረሻ የእድገት ተዋረድ ላይ ደርሰው ከነበሩ ሙያተኞች መካከል በያዙት ሙያ ከ10 ዓመት በላይ አገልግሎት ያለው ወይም ከጀማሪ ስፔሻሊስቶች በስተቀር በቀደሞው ምደባ ፐሣ-6/1 ደረጃ ላይ ደርሶ በሙያው አንድ ዓመትና በላይ በማገልገል ቢያንስ 11 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው የጤና ባለሙያ በአዲሱ የሙያው እድገት መሰላል የሚጨረሻው ተዋረድ/ተዋረድ IV/ ላይ ተመድቦ በደረጃው 3ኛ እርከን ላይ የተመለከተውን ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

22) የከፍተኛ ትምህርት የአካዳሚክ ባለሙያዎች፣ የቴክኒካል ረዳቶች፣ ተመራማሪዎች፣ መደበኛ መምህራን፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናአሰልጣኞች፣ ኢንስትራክተሮች እና ሌሎች ለካርየር ዕድገትበተዘጋጁ ልዩ መስፈርቶች ይጠቀሙ በነበሩ ተቋማት ያሉ ሙያተኞቻቸው በነበሩበት ደረጃ ያለወድድር ከተደለደሉ በኋላ ወደ ቀጣዩ የእድገት መሰላል የሚሸጋገሩት ለደረጃው የተቀመጡ ነባር መስፈርቶችን ሲያሟሉ ነው፡፡

23) የኮሌጅ የትምህርት ደረጃና በታች የትምህርት ዝግጅት በሚጠይቁ የሥራ መደቦች ላይ የሥራ መደቡ የሚጠይቀው የት/ደረጃ ሳይኖረው በልዩ ሁኔታ ለአንድ ጊዜ እንዲደለደሉ ጳጉሜ 2 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር ፐሰሚ/30/ጠ10/91/17 በተጻፈ ደብዳቤ ሸኝነት በተላከው ማብራሪያ መሠረት የተደለደለ ሠራተኛ የተመደበበት ደረጃ የሚያስገኘውን የመሸጋገሪያ ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

24) በድልድል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 7.8 መሠረት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ከደረጃ I እስከ ደረጃ V ሠልጥነው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው ባለው የትምህርት ምስክር ወረቀት ለአንድ ጊዜ የተደለደለ ሠራተኛ የተመደበበት ደረጃ የሚያስገኝለትን የመሸጋገሪያ ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

25) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) መሰረት በደመወዝ ስኬል ሽግግር የሚገኘው የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ መጠን ለሶስት ተካፍሎ መሸጋገሪያ ደመወዝ እንዲከፈለው የተደረገ ሰራተኛ እስከ ሰኔ 2013 ዓ.ም ድረስ ከደመወዙ ላይ ታክስ የሚቀነሰው ለበጀት አመቱ ከተፈቀደለት መሸጋገሪያ ደመወዝ ላይ ነው፡፡

26) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 (ለ) ቢኖርም ከ2012 እስከ 2014 የበጀት አመቶች ባለው ጊዜ ወስጥ በጡረታ ከስራ ከሚለሉ ሰራተኞች መካከል፡-

ሀ) ከሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም አስከ ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ወስጥ በጡረታ ከስራ የሚለይ ሰራተኛ ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል ሲሸጋገር ሙሉ የደመወዝ ማሻጋገሪያውን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ለ) ከሀምሌ 2012 ዓ.ም አስከ ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም ባለው ጊዜ ወስጥ በጡረታ ከስራ የሚለይ ሰራተኛ ከሀምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ለተመደበበት ደረጃ የተወሰነውን የደመወዝ ማሻጋገሪያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3 ማስረት ከተከፈለው በኋላ የ2013 የበጀት አመት ሙሉ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያውን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 26 (ሀ) እና (ለ) የተመለከተው የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ እድሜው 60 አመት ሳይሞላው በፍቃዱ በጡረታ ከስራ የሚለይ ሰራተኛን አይመለከትም፡

## 7.የደረጃ ዕድገት የሚያገኙ ሠራተኞችን እና አዲስ ተቀጣሪን በሚመለከት

የነጥብ የሥራ ምዘናና ሥርዓት ከክፍያ ጋር ከተሳሰረ በኋላ በቀጣይ ሙሉ ክፍያውን በሶስት እኩል ማጠን እንዲከፈለው የተደረገ ሠራተኛ በያዘው ደረጃ ላይ ሌላ ሠራተኛ በደረጃ ዕድገት ወይም በቅጥር በአዲሱ የደመወዝ ስኬል ላይ ሲመደብየደመወዝስኬል ማስተካከያው ደረጃ በደረጃ እንዲከፈላቸው ከተደረጉ ሌሎች ነባር ሠራተኞች የክፍያ ማጠን መብለጥ ስለሌለበት፡-

### 1) የደረጃ ዕድገት የሚያገኙ ሠራተኞችን በሚመለከት

ይህ የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ አፈጻጸም መመሪያ ከጸደቀበት ወር ቀጥሎ እስከ ሰኔ ወር 2013ዓ.ም ድረስ የደረጃ ዕድገት ካገኙ ሠራተኞች መካከል በደረጃ ዕድገት ስም ያገኘው የገንዘብ ማጠን፡-

ሀ) እስከ ብር 1000 ከሆነ ሠራተኛው የደመወዝ ልዩነቱን የደረጃ ዕድገት ካገኘበት ወር መጀመሪያ ቀን ጀምሮ ይከፈለዋል፡፡

ለ) ከብር 1000 በላይ ሆኖ በ2012ዓ.ም የበጀት ዓመት የደረጃ ዕድገት ካገኘ የደረጃ ዕድገት የደመወዝ ልዩነቱን ለሶስት በማካፈል ወጠቱን እየተከፈለው ባለው የወር ደመወዝ ላይ

- ካደገበት ወር እስከ ሰኔ 2012ዓም ድረስ 1/3ኛ፣
- ከሀምሌ ወር 2012 ዓም እስከ ሰኔ 2013ዓ.ም ሁለተኛውን 1/3 እና
- ከሀምሌ 2013ዓ.ም ጀምሮ የመጨረሻውን 1/3ኛ

የደመወዝ ማስተካከያ በመጨመር የሠራተኛው ደመወዝ እንደሁኔታው ወደ ተመደበበት ደረጃ የመነሻ ወይም የእርከን ደመወዝ ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡

ሐ) ከብር 1000 በላይ ሆኖ በ2013ዓ.ም የበጀት ዓመት የደረጃ ዕድገት ካገኙ የደረጃ ዕድገት የደመወዝ ልዩነቱን ለሁለት በማካፈል ወጠቱን እየተከፈለው ባለው የወር ደመወዝ ላይ

- ካደገበት ወር እስከ ሰኔ 2013 ዓ.ም ድረስ ½ኛ የደረጃ እድገት ልዩነቱን በመጨመር እና
- ከሀምሌ ወር 2013 ዓ.ም ጀምሮ የሚቀረኛውን ½ኛ የደረጃ ዕድገት ልዩነቱን በመጨመር

የሠራተኛው ደመወዝ ወደ ተመደበበት ደረጃ የመነሻ ወይም የእርከን ደመወዝ ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡

መ) ከሀምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የደረጃ ዕድገት የሚያገኝ ሠራተኛ ለሚያድግበት ደረጃ የተወሰነውን የመነሻ ወይም የእርከን ደመወዝ ካደገበት ወር መጀመሪያ ቀን ጀምሮ ይከፈለዋል፡፡

2) **አዲስ ተቀጣሪን በሚመለከት**

በዚህመመሪያአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 3የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ማግስት ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ወስጥ፡-

ሀ) ከደረጃ ከደረጃ I እስከ ደረጃVII ባሉ ደረጃዎች የተቀጠረ ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደረጃ መነሻ ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ለ) ከደረጃVII በላይ ባሉ ደረጃዎች የሚቀጠር ሠራተኛ በተቀጠረበት የሥራ ደረጃና ከተቀጠረበት ደረጃ በአንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ በሚገኝ ደረጃ መካከል ያሉ ሶስት የእርከን ልዩነቶችን በየበጀት ዓመቱ ዝቅ ባለው ደረጃ የመነሻ ደመወዝ ላይ አንድ አንድ እርከን በመጨመር የወር ደመወዝ እንዲከፈለው በማድረግ ከሀምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የተቀጠረበትን ደረጃ የመነሻ ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**ምሳሌ 1**ደረጃ XV የመነሻ ደመወዝ ብር 10150፣ የደረጃ XIV መነሻ ደመወዝ ደግሞ ብር 9056 ቢሆን፣ እንዲሁም የዚሁ ደረጃ 1ኛ እርከን ደመወዝ ብር9420፣ የደረጃው የ2ኛ እርከን ደመወዝ ብር 9785 እና የ3ኛው እርከን ደመወዝ ብር 10150 ቢሆን አዲሱ የደመወዝ ስኬል ተግባራዊ ከሆነበት ቀን ማግስት ጀምሮ በደረጃ XV የተቀጠረ ሠራተኛ የተቀጠረበት ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

- እስከ ሰኔ 2012 ዓ.ም ድረስ ከተቀጠረበት ደረጃ ደረጃ ዝቅ ብሎ በሚገኘው የደረጃ XIV መነሻ ደመወዝ 9056 ላይ አንድ እርከን በመጨመር የደረጃው 1ኛ እርከን ደመወዝ የሆነውን ብር 9420፣

- በሁለተኛው የበጀት ዓመትከሀምሌ 2012ዓ.ም እስከ ሰኔ 2013ዓ.ምየደረጃ XIV 2ኛ እርከን ደመወዝ የሆነውን ብር 9785፣
- በሶስተኛው የበጀት ዓመትከሀምሌ 2013ዓ.ም ጀምሮ የተቀጠረበት ደረጃ XV የማሻ ደረጃ የማሻ ደመወዝ የሆነውን ብር 10150፣

እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ሐ) ከሀምሌ 1 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓም ድረስ የሚቀጠር ሠራተኛ ከተቀጠረበት ደረጃ በአንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ የሚገኝ የሶስት እርከን የገንዘብ ማጠንን ለሁለት በማካፈል ከተቀጠረበት ደረጃ በአንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ በሚገኝ የማሻ ደመወዝ ላይ በመደመር የመጀመሪያው ዙር ደመወዙ በየወሩ የሚከፈለው ሲሆን፣ ከሀምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የቀረውን ገንዘብ በሚከፈለው ደመወዝ ላይ በሚጨመር የተቀጠረበትን ደረጃ የማሻ ደመወዝ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

**ምሳሌ 2** ከላይ በምሳሌ አንድ ላይ በተጠቀሰው ደረጃ XV ላይ በ2013ዓ.ም የበጀት ዓመት /ከሀምሌ 1 ቀን 2012ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2013ዓ.ም/የተቀጠረ ሠራተኛ **የተቀጠረበት ደረጃ እንደተጠበቀ** ሆኖ ከተቀጠረበት ደረጃ በአንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ በሚገኘው የደረጃ XIV ማሻ ደመወዝን ከደረጃው የ3ኛ እርከን በመቀነስና ልዩነቱን ለሁለት በማካፈል /10150-9056 = ብር 1094/ ስለሚሆን ብር 1094ን ለሁለት በማካፈል /1094/2/ የተገኘውን ብር 547 ደረጃ XIV ማሻ ደመወዝ በሆነው ብር 9056 ላይ በመደመር ብር /9056 + 547/ ብር 9603 እስከ ሰኔ 2013ዓ.ም ድረስ እንዲከፈለው ይደረጋል፡፡

ከሀምሌ 1 ቀን 2013ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ ብር 9603 ላይ ቀሪውን 547 በሚጨመር /9603 + 547 = 10150/ የሠራተኛው ደመወዝ የተቀጠረበት ደረጃ XV ማሻ ደመወዝ በሆነው ብር 10150 ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡

መ) ከሀምሌ 1 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ የሚቀጠር ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደረጃ የማሻ ደመወዝ ከተቀጠረበት እለት ጀምሮ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

## 8. ተፈፃሚነት ስለሚይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና የተለመደ አሠራር በዚህ መመሪያ ወስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 9. ተጠያቂነት

የዚህ መመሪያንድንጋጌዎች በመተላለፍ ተመዝኖ ደረጃ ባልወጣለት የሥራ መደብ ላይ የሠራተኛ ድልድል የሚፈጽም ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 10. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለኮሚሽኑ እየቀረበ ወሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል።

## 11. የመመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**በዛብህ ገብረየስ**

**የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን**

**ኮሚሽነር**

**አባሪአንድ የማግሥት ሠራተኞች የደመዝ ስኬል**

**(ሀምሌ2011 ዓ.ም)**

| ደረጃ | መነሻ ደመዝ | የእርከን ደመዝ | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| I. | **1100** | **1174** | **1253** | **1338** | **1428** | **1523** | **1624** | **1731** | **1843** | **1958** | **2079** |
| II. | **1338** | **1428** | **1523** | **1624** | **1731** | **1843** | **1958** | **2079** | **2208** | **2344** | **2487** |
| III. | **1624** | **1731** | **1843** | **1958** | **2079** | **2208** | **2344** | **2487** | **2638** | **2799** | **2969** |
| IV. | **1958** | **2079** | **2208** | **2344** | **2487** | **2638** | **2799** | **2969** | **3150** | **3333** | **3526** |
| V. | **2344** | **2487** | **2638** | **2799** | **2969** | **3150** | **3333** | **3526** | **3729** | **3934** | **4150** |
| VI. | **2799** | **2969** | **3150** | **3333** | **3526** | **3729** | **3934** | **4150** | **4379** | **4609** | **4851** |
| VII. | **3333** | **3526** | **3729** | **3934** | **4150** | **4379** | **4609** | **4851** | **5098** | **5358** | **5626** |
| VIII. | **3934** | **4150** | **4379** | **4609** | **4851** | **5098** | **5358** | **5626** | **5907** | **6193** | **6481** |
| IX. | **4609** | **4851** | **5098** | **5358** | **5626** | **5907** | **6193** | **6481** | **6773** | **7071** | **7377** |

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| X. | 5358 | 5626 | 5907 | 6193 | 6481 | 6773 | 7071 | 7377 | 7690 | 8017 | 8354 |
| XI. | 6193 | 6481 | 6773 | 7071 | 7377 | 7690 | 8017 | 8354 | 8705 | 9056 | 9420 |
| XII. | 7071 | 7377 | 7690 | 8017 | 8354 | 8705 | 9056 | 9420 | 9785 | 10150 | 10521 |
| XIII. | 8017 | 8354 | 8705 | 9056 | 9420 | 9785 | 10150 | 10521 | 10906 | 11305 | 11719 |
| XIV. | 9056 | 9420 | 9785 | 10150 | 10521 | 10906 | 11305 | 11719 | 12148 | 12579 | 13013 |
| XV. | 10150 | 10521 | 10906 | 11305 | 11719 | 12148 | 12579 | 13013 | 13462 | 13926 | 14400 |
| XVI. | 11305 | 11719 | 12148 | 12579 | 13013 | 13462 | 13926 | 14400 | 14890 | 15396 | 15912 |
| XVII. | 12579 | 13013 | 13462 | 13926 | 14400 | 14890 | 15396 | 15912 | 16437 | 16979 | 17531 |
| XVIII. | 13926 | 14400 | 14890 | 15396 | 15912 | 16437 | 16979 | 17531 | 18092 | 18671 | 19252 |
| XIX. | 15396 | 15912 | 16437 | 16979 | 17531 | 18092 | 18671 | 19252 | 19850 | 20468 | 21092 |
| XX. | 16979 | 17531 | 18092 | 18671 | 19252 | 19850 | 20468 | 21092 | 21725 | 22361 | 23005 |
| XXI. | 18671 | 19252 | 19850 | 20468 | 21092 | 21725 | 22361 | 23005 | 23654 | 24305 | 24961 |
| XXII. | 20468 | 21092 | 21725 | 22361 | 23005 | 23654 | 24305 | 24961 | 25622 | 26288 | 26959 |

**ቁጥር ሰሰኮ30/ጠ10/92/180**

**ጳጉሜ 5 ቀን 2011ዓ.ም**

**በዝርዝሩ ለተመለከቱት**

**ባ ሉ በ ት**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት **ነሀሴ** 4 ቀን 2011 ዓ.ም ባካሄደው አምስተኛ የምርጫ ዘመን 16ኛአስቸኳይ ስብሰባ መንግሥት ከሐምሌ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ የነጥብ ሥራ ምዘና ውጤትን በመንግስት መሥሪያ ቤቶች ለመተግበር የተዘጋጀው የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ ተግባራዊ እንዲሆን ወስኗል፡፡

ምክር ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ባካሄደው ስብሰባ ያሳለፋቸውን ወሳኔዎችና የደመወዝ ስኬል ማሻጋገሪያ ሂደቱን ለማስፈጸም የተዘጋጀውን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ከዚህ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልጻለን፡፡

**ከሰላምታ ጋር**

ግልባጭ

- ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለምክትል ኮሚሽነር ጽ/ቤት
- ለአደረጃጀት የሥራ ምዘናና የክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ህጎች ጥናትና ስርፀት ዳይሬክቶሬት

የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

አዲስ አበባ